# ለበውቀቱ ደጋፊዎች መልስ!

ባለፈው ሳምንት "በውቀቱ ሥዩምን ጸበል ሒድ ብየው እሽ ብሎኝ ነበር፤ በእግዚአብሔር አለማመን (atheism) እና ፍልስፍና ምንድን ነው?" በሚል ርእስ ስለ በውቀቱና "እግዚአብሔር የለም!" ስለሚሉ ሰዎች አንድ ጽሑፍ መጻፌ ይታወሳል፡፡ በዚህ ጽሑፍ ላይ ጥቅማችን ተነካ የሚሉ ወገኖች ከተለያየ አቅጣጫ በተለያየ ድረገጽ ላይ እንዲሁም በግል ተመሳሳይ ግን በርካታ ቅሬታዎችና አስተያየቶች ደርሰውኛል፡፡

እኔ የጻፍኩት ጽሑፍ በቂና የተብራራ መስሎኝ ነበር፡፡ የረዘመውም በዚያ ምክንያት ነው፡፡ ከግብረ መልሱ እንደተረዳሁት ግን ብዙዎችን አልገባቸውም፤ ወይ ደግሞ ይዘውት የቆዩትን አቋም በአንድ ቀን መለወጡ ከብዷቸው ይሁን ወይም ሊያስተውሏቸው የሚገባቸውን ቀላል ቀላል ነገሮች ሳያስተውሉ ቆይተው አሁን ስጠቁማቸው ሊያስተውሏቸው ይገባ እንደነበር መረዳታቸው አሳፍሯቸው ካፈርኩ አይመልሰኝ ብለው ይሁን ወይም ደግሞ አሁንም ሊገባቸው ስላልቻለ አላውቅም መልሱ እዚያው ጽሑፉ ውስጥ እያለ ጥያቄ ያነሡ ሰዎች በርካታ ናቸው፡፡

ለማንኛውም እንዳሉት ጽሑፉ ላይ ያለው በቂ ካልሆነ ለጥያቄያቸው መልስ የመመለስ ግዴታ አለብኝና ግልጽ አድርግልን ተብለው ለተጠየቁ ጥያቄዎችና ለሌሎች አስተያየቶች እንደሚከተለው መልሻለሁ፡-

ከአስተያየቱ ስንጀምር ብዙዎቹ ተግሳጽና ዘለፋ መጨመሬን አልወደዱትም፡፡ እነሱ እኔን "ለምን እንዲህ አደረክ?" እያሉ ግን እነሱም እኔን በመዝለፍ ይሄንን ማለታቸው ነው ግራ አጋቢው ነገር፡፡ ወዳጆችም ቢሆኑ ተግሳጽና ዘለፋ መጨመሬን አልወደዱትም፡፡

ግን ግን ቆይ እስኪ! እኔ ጽሑፉ ላይ መዝለፍ፣ መሳደብ "የጽድቅ ሥራ ነው፤ እኔም ጻድቅ ነኝ" ብያለሁ እንዴ? ለምንድን ነው ያልተጻፈ የሚያነቡት? እኔ ጻድቅም ነኝ ቁስም ነኝ አላልኩም አይደለሁምም፡፡

እኔ ያደረኩት ነገር ምንድን ነው? እናት አባቶቻችን ሲያደርጉት እንደኖሩት እንደ ዜጋና እንደ ክርስቲያን የሀገሬና የቤተክርስቲያኔ ጠላት የቃጣውን ጥቃት ነው የተከላከልኩት፡፡ ይሄንን የማድረግ ዜጋዊም ሆነ ክርስቲያናዊ ግዴታ አለብኝና፡፡ እናት አባቶቻችን በጠላት ላይ በመዝመት ይህችን ሀገርና ሃይማኖት እስከ ሕይዎት መሥዋዕትነት ድረስ በመክፈል እንዳቆዩልን የሚዘነጋ አይመስለኝም፡፡

እንዲህ ያሉኝን ሰዎች "ምን ታዘብካቸው?" ብትሉኝ በውቀቱ በባንዳነት አድሮ ሀገርንና ቤተክርስቲያንን እንዲያ ሲያጠቃ፣ እንዲህ ባለ ቅጥ ያጣ ስድነት የድንቁርናና ድፈረት ሊታሰብ የማይገባ ስሕተት ሲፈጽም ምንም ያላለው አንደበታቸው እኔ አንድ ውርጋጥ ባንዳ በመዝለፍ በመገሰጼ እንዲህ መንጫጫታቸውን እጅግ በጣም ነበር የታዘብኩት፡፡ ስለሆነም እንዲያው የሚሉት ቢያጡ እኔን ለመቃወም ያክል ይሄንን አሉ እንጅ ጉዳዩ ይሄ አይደለም ጉዳዩ "ለምን ተነካን!" ነው፡፡ እነሱ ለተከበሩና ለማይገባቸው ታላላቅ አባቶች ጸያፍ ቃላትን ሲሰጡ ምንም ያልመሰላቸው ምንም ለሆኑት ለነሱ በብልግናቸው ምክንያት የሚገባቸው ስም ሲሰጣቸው ግን አንገበገባቸው አበሳጫቸው አንጫጫቸው፡፡ አይገርማቹህም?

ሲጀመርም ቢሆን እኔ ስድብና ዘለፋ እግዚአብሔርን እንደሚያስቀይም ኃጢአትም እንደሆነ አጥቸው አይደለም፡፡ ነገር ግን ብዙዎቻቹህ "መቸና ማን ላይ ሲሆን ነው እግዚአብሔርን የሚያስቀይመው መስደምብ መግደልም የሚያስኮንነው?" የሚለውን የምታውቁ አልመሰለኝም፡፡

እናት አባቶቻችን ይሄንን ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ አድዋ ላይም ሆነ ከዛም በፊት ከዚያም በኋላ ድንበር ገፍቶ ከመጣ ጠላት ጋር እየተናነቁ ሲገሉም ሲሠውም ኃጢአት እያደረጉ እንደሆነ እያሰቡ ይመስላቹህል ያንን ያደርጉ የነበሩት? ካህናቱስ የቃልኪዳኑን ታቦት ተሸክመው አብረው በመሰለፍ "እግዚአብሔር ይፍታሕ! ግባ በለው!" እያሉ እያጀገኑ ሲያዋጉ የማይገባ ነገርን ወይም ኃጢአት እያደረጉ ይመስላቹህል እንዴ? እንዳይመስላቹህ!!!

በእርግጥ ጥቂት ያልሆኑ ይሄንን ያደረጉ እናት አባቶቻችንም የሀገር ጉዳይ ሆኖባቸው ስላልቻሉ "አትግደል!" የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ እንዳደረጉት ያስቡ ነበር እንጅ ያደረጉት ነገር ኃጢአት እንዳልሆነ በማሰብ አያደርጉትም ነበር፡፡ እውነቱ ግን የእግዚአብሔር ቃል ይሄንን እንዲያደርጉ ይፈቅድላቸዋል፡፡ እንዴት? ብትሉ ነገሩ እንዲህ ነው፡-

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል "ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና" ይላል ቅዱስ ቃሉ ሮሜ. 13፤1-4

ይሄ ማለት ምን መሰላቹህ? እንዲህ ሲል ለሁሉም ለመጣ ለሔደው ሁሉ ብቻ ገዥ ሆኖ ለተሾመው ለመጣባቹህ ሁሉ ሰጥ ለበጥ ብላቹህ ተገዙ ማለት ነው የሚመስላቹህ? በፍጹም! እንደዛ ማለቱ አይደለም:: በሃይማኖት ለሚመስሏቹህ፣ ሃይማኖታቹህን ሀገራቹህን

ለሚጠብቁላቹህ፣ ከጠላቶቻቹህ ጋር ለማይተባበሩ፣ ሃይማኖታቹህን ጣሉ ግብራቹህን ለውጡ ለማይሏቹህ፣ ሃይማኖታቹህን ሲያጠፉ ለማያሴሩባቹህ ማለት ነው፡፡

አለዛማ እኮ እነ ዲዮቅልጥያኖስን፣ እነ መክስምያኖስን በሀገራችን ደግሞ እነ ዮዲት ጉዲትን፣ እነ ግራኝ አሕመድን፣ እነ ፋሽስት ጣሊያንን እየተቀበልንና ያሉንን እየፈጸምን ማለትም "ሃይማኖት ለውጡ! ጣዖት አምልኩ!" ሲሉ እሺ ብለን እየለወጥን ጣዖት እያመለክን "ምግባራቹህን ጣሉ!" ሲሉን እሺ ብለን ምግባራችንን እየጣልን መገዛት ነበረብን ማለት ሊሆን እኮ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ እግዚአብሔርን የሚያስቀይም፣ የሚያስከፋ፣ የሚያስቆጣ የገሐነም ፍርድም የሚያሰጥ ድርጊት እንጅ እግዚአብሔርን የሚያስደስት የጽድቅ ሥራ እንዳልሆነ ታውቃላቹህ ብየ እገምታለሁ፡፡

እናም እነኝህ እኛን የሚመስሉ ገዥዎቻችን ወይም መንግሥታቶቻችን ጠላትንም ሆነ በባንዳነት አድሮ የሀገርንም ሆነ የሃይማኖትን ጥቅም የሚጋፋውን የሚጻረረውን፣ ለሞት የሚያበቃ ወንጀል የፈጸመውን ሁሉ በሞት ቢቀጡት ኃጢአት አይሆንባቸውም፡፡ በጠቀስኩላቹህ ጥቅስ ላይ ቁጥር አራት ላይ ያለውን ቃል ልብ ብላቹህታል? "...በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል <u>የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና</u>" ነው ያለው፡፡ አያቹህ? ክፉ አድራጊውን በመበቀሉ በመቅጣቱ "የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው" ተባለ እንጅ ነፍስ አጥፍቷል ተብሎ ኃጢአተኛ ነው አልተባለም፡፡ ድርሳነ ሚካኤልም ይሄንን ይዞ ነው "ወለ ሕዝባዊያንሰ ብውኀ ሎሙ እም ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይቅትሉ በፍትሕ ለዘይደልዎ ሞት! ፤ከሕዝብ ወገን የሆኑት (ክህነት የሌላቸው) ሞት ለሚገባው በፍትሕ ይገድሉ ዘንድ ከእግዚአብሔር ተፈቅዶላቸዋል!" ያለው፡፡

ለዚህም እኮነው ዐፄ ምኒልክ አድዋ ሲዘምቱ በአዋጃቸው ላይ ኃጢአት እንዳልሆነ በተረዳ ልበ ሙሉነት "… ሀገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት!" ሲሉ አዋጃቸውን ያስነገሩትና ሕዝባቸውን ያዘመቱት፡፡ በዚህ ምክንያት የሚደረግ ጦርነት ጽድቅ እንጅ ኃጢአት እንዳልሆነ ስለሚያውቁ፡፡ አለዛማ ሀገርንም ሃይማኖትንም አስረክበው ቁጭ አይሉም ነበር እንዴ? ቅዱስ ጊዮርጊስም ከአምላክ ተልኮ የተራዳን እኮ ለዚህ ነው፡፡ ጣሊያኖች ምስክርነት ሰጥተው የለም እንዴ! ከአርበኞች አንዱ መስሏቸው ጦርነቱ ካለቀ በኋላ ምርኮኞቹ "ስንተኩስበት የማይሞተው በነጭ ፈረስ ላይ ሆኖ በሰይፉ እየቀላ ሲፈጀን የነበረው ሰውየ ማን ነው? የታለ?" ብለው ነበር፡፡

ክርስትና እራስን "ለእርድ ማቅረብ" ማለት የሚመስላቹህና ይሄንንም የምትሰብኩ አባቶችና ወንድሞች ካላቹህ እርማት ውሰዱ፡፡ ክርስትና እንዲህ አይደለም! በእርግጥ ክርስትና የፍቅር ሃይማኖት ነው፡፡ ይሄ ማለት ግን "በፍቅር ካልሆነ በግፍ በኃይል የሚያደርገው አንድም ነገር የለም!" ማለት እንጅ በግፍ ለሚመጡበት አረማውያን ለመሥዋዕት እንደሚነዳ በግ በዝምታ ወደ መታረጃው የሚነዳ መንጋ ማለት አይደለም፡፡

አዎ! ክርስቶስ በወንጌሉ ክፉውን በክፉ እንዳንቃወም አዞናል፣ ቀኝ ጉንጫችንን ለሚመታን ግራችንንም እንድናዞርለት፣ እጀ ጠባባችንን ለሚወስድብን መጎናጸፊያችንን እንድንጨምርለት፣ አንድ ምእራፍ እንድንሔድ ለሚያስገድደን ሁለተኛውን ምእራፍ ፈቅደን እንድንሔድለት አዞናል፡፡ ይሄንን ሲል ግን ጠላት ዲያብሎስ አንድ በግ ሲነጥቃቹህ ሁለተኛውን ጨምሩለት፣ ጥምቀተ ባሕሩን

ሲወስድባቹህ መስቀል አደባባዩንም ጨምሩለት፤ ይሄንና ይሄንን የመሰለ ጅልነት አድርጉ ማለቱ እንዳልሆነ ሁላችንም መረዳት የምንችል ይመስለኛል፡፡

ስለሆነም ይህ አምላካዊ ትዕዛዝ ቅድመ ሁኔታና መቸት አለው ማለት ነው፡፡ ባጭሩ ሃይማኖትንና ሀገርን በተመለከተ ጉዳይ ላይ ይሄንን አምላካዊ ትዕዛዝ እንድንፈጽም ፈጽሞ አልታዘዝንም፡፡ የሚመስላቹህና ሳይገባቹህ ሰው ጅል እንዲሆን የምትሰብኩ አባቶችና ወንድሞች በክርስትና ላይ ያላቹህን የተሳሳተ መረዳት አስተካክሉ!

ስለሆነም በመሳደቤ አይግረማቹህ አይድነቃቹህ እሽ? ጥፋት ኃጢአት የሠራሁም አይምሰላቹህ፡፡ መታየት ያለበት ነጥብ ማንን ነው የተሳደበው? ማንን ነው የገደለው? ማንን ነው ያጠቃው? የሚለው ነጥብ ነው ነገሩን ኃጢአት ወይም ጽድቅ የሚያደረገው እሽ ወገኖቸ?

ወደ ጥያቄዎቻቹህ ስገባ፡- "በሰው ላይ ያደረ ሰይጣን… ብሎ ገሰጻኝና ነው ከክህደት የተመለስኩት ብለህል፤ ሰይጣን እግዚአብሔርን ያስከዳን ኃጢአት ያሥራል እንጅ ሰብኮ መክሮ ገስጾ ይመልሳል እንዴ?" ስትሉ ጠይቃቹሀል፡፡ ይሄ ብቻ አይደለም ኃጢአት የሚያሠራው የሚያሳስተው የሚያሰናክለው እሱ ሆኖ ሳለ እንደገና ደግሞ ዞሮ ጻበል ላይና በቅዱሳን ሲያዝ የሰውን ኃጢአት እየዘረዘረ ሰውን ማሸማቀቁ ደርሶ ሰባኪነኝ ተቆርቋሪ ነኝ ማለቱም ይገርመኛል፡፡ ማን ሆነና እንደዛ ያስደረገን? አንድ ጊዜ ባንድ ሰው ላይ ያደረውን ክፉ መንፈስ እንዲህ ብለው እንዴት እንዳፈጠጠብኝ ልነግራቹህ አልችልም፡፡

ነገሩ ምን መሰላቹህ፡- ወንጌል ላይ እንዲህ የሚል ቃል አለ "…ጊዜ አጋንንት ያደሩበት አንድ ሰው ከከተማ ወጥቶ ተገናኘው፥ ከብዙ ዘመንም ጀምሮ ልብስ ሳይለብስ በመቃብር እንጂ በቤት አይኖርም ነበር። ኢየሱስንም ባየ ጊዜ ጮኾ በፊቱ ተደፋ በታላቅ ድምፅም። የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳትሣቀየኝ እለምንሃለሁ አለ። ርኵሱን መንፈስ ከሰውዬው እንዲወጣ ያዘው ነበርና። ብዙ ዘመንም ይዞት ነበርና፥ በሰንሰለትና በእግር ብረትም ታስሮ ይጠበቅ ነበር፤ እስራቱንም ሰብሮ በጋኔኑ ወደ ምድረ በዳ ይነዳ ነበር። ኢየሱስም። ስምህ ማን ነው? ብሎ ጠየቀው። እርሱም ብዙዎች አጋንንት ገብተውበት ነበርና። ሌጌዎን አለው። ወደ ጥልቁም ሊሔዱ እንዳያዛቸው ለመኑት።

በዚያም በተራራው የብዙ እሪያ መንጋ ይሰማሩ ነበር፤ ወደ እነርሱም ሊገቡ እንዲፈቅድላቸው ለመኑት፤ ፈቀደላቸውም። አጋንንትም ከሰውዬው ወጥተው ወደ እሪያዎች ገቡ፥ መንጋውም ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና ሰጠሙ። እረኞችም የሆነውን ባዩ ጊዜ ሸሽተው በከተማውና በአገሩ አወሩት። የሆነውን ነገር ሊያዩ ወጥተውም ወደ ኢየሱስ መጡ፥ አጋንንትም የወጡለትን ሰው ለብሶ ልቡም ተመልሶ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጦ አገኙትና ፈሩ" ሉቃ. 8፤27-39

ሌላም ቦታ ላይ " በዚያን ጊዜም በምኩራባቸው ርኵስ መንፈስ ያለው ሰው ነበረ፤ እርሱም። የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ፥ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ። ኢየሱስም ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው። ርኵሱም መንፈስ አንፈራገጠውና በታላቅ ድምፅ ጮኾ ከእርሱ ወጣ" ማር. 1፤23-26

አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአንሔር ልጅ እግዚአብሔር እንደሆነ እንዳያምኑ ያደረጋቸው ልባቸውን ያደነደነው እርኩስ መስፈስ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሄ እርኩስ መንፈስ ደግሞ እንደገና ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዴት ባለ መፍራትና መንቀጥቀጥ እንደመሰከረ ከጥቅሶቹ አንብባቹሀል፡፡ እንግዲህ የሱ ነገር ይሄው ነው ሲያዝ እውነቱን ይናገራል ይለፈልፋል እንደሱ ያለ ሰባኪ የለም፡፡ ካልተያዘ ደግሞ የሰው ልጆችን በሕመም፣ በክህደት፣ በጥርጣሬ፣ በስስት፣ በሚርት፣ ጣኦትን በማምለክ፣ ገንዘብን በመውደድ፣ በዝሙት፣ በርኩሰት፣ በመዳራት፣ በጥል፣ በክርክር፣ በቅንዓት፣ በቁጣ፣ በአድመኛነት፣ በመለያየት፣ በመናፍቅነት፣ በምቀኝነት፣ በመግደል፣ በስካር፣ በዘፋኝነት እንደሚያሰቃይ ታውቃላቹህ፡፡ ሲያዝ ደግሞ እንደተማረከ ወታደር ማለት ነው፡፡ ወታደር ሲማረክ ነፍሱን ለማዳን የማይቀበጣጥረው ነገር የለም አይደል? እንደዚያ ሆኖ ነው ነገሩ፡፡

ይሁን እንጅ በጣም የሚገርማቹህ ሰይጣን በጸበል ሲያዝ ሰይጣን ምንጊዜም ቢሆን ሰይጣን አይደል? ተያዘ በቁጥጥር ስር ዋለ እንጅ "ከሰይጣንነት ወደ መልአክነት ተለወጠ የክፋት ሥራውን ተወ" ማለት አይደለምና ተይዞ እየለፈለፈም ይዋሻል፣ ሰውን ከሰው ጋር በማጋጨት ጥቅሙን ለማግኘት በሚናገረው ነገር ሴራ ይሸርባል፡፡ ለምሳሌ ዘመድን ከዘመድ፣ ባልን ከሚስት ለማጋጨት "እከሊት ናት እከሌ ነው ሚርት መተት ያደረገችብሽ ያረገብህ!" እያለ ያላረጉትን ሰዎች ሁሉ ያነካካል በነገር ያጣምዳል፡፡ ተፈጥርቆ ሲያዝ ግን ያን ያደረገውን ጠንቋይና አስደራጊውን ክፉ ሰው ካሉበት ሀገር እያንደፋደፈ ሁሉ ያመጣቸዋል፡፡

በገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ምን ብሎ ዋሸ መሰላቹህ "ለአዳም ለፍጡሩ አልሰግድም ስላልኩ ነው እግዚአብሔር ከሥልጣኔ ሽሮ ያዋረደኝ" ብሎ ዋሸ፡፡ ያለው ነገር መመዝገብ አለበትና ይሄ ተመዝግቧል፡፡ በድርሳነ ሚካኤል ላይ ግን ሰይጣን የተዋረደው የተሻረው በመጀመሪያዋ ቀን በዕለተ እሑድ ስለሆነና አዳም የተፈጠረው በስድስተኛው ቀን በመሆኑ እንዲያ ማለቱ ከሐሰት አባትነቱ የተነሣ ሐሰቱን መሆኑ ተጽፏል፡፡

እናም ሰይጣን የተናገረው የለፈለፈው ሁሉ እውነት አይደለምና በሚናገረው ነገር ላይ ጥንቃቄ መውሰድ ያሻል፡፡ በተቻለው መጠን በሚናገረው ነገር እንደምንም እያለ ጥቅሙን ለማስጠበቅ ጥረት ያደርጋል፡፡ ካህናትና ምዕመናን ማተኮር ያለባቹህ ፈውሱ ላይ ነው እንጅ "ምን አለ? እስኪ ምን ይናገራል?" ብላቹህ ጆሮ ከሰጣቹህት ሦስት ነገር ይናገር እንደሆነ ሁለቱ ሐሰትና ለራሱ የሚጠቅም ነገር ነው የሚናገረው፡፡ ከሚናገረው ነገር የትኛው እውነት የትኛው ሐሰት እንደሆነ መርምሮ ለመድረስ በጣም ከባድ ስለሆነ ቢቻላቹህ እንዲለፈልፍ ባትፈቅዱለትና ዝም ብሎ እንዲወጣ ብታደርጉ ነው የሚሻለው፡፡ ለዚህም ነው ኢየሱስ ጋኔን በሚያስወጣበት ጊዜ ሲለፈልፍ ሲቀባጥር "ዝም በል!" በማለት የሚገሥጸው ማር. 1፤25፡፡

ሌላው ጥያቄ ምንድን ነው፡- ብዙዎቻችሁ በፍጹም በውቀቱ ሀገርንም ቤተክርስቲያንንም አላጠቃም በማለት በከንቱ ተሟግታቹህል፡፡ የመጽሐፉን ትዝብት በሌላ ጽሑፍ እንደማቀርብ ስለገለጽኩ አንዳንድ ነገሮችን ከመግለጽ ተቆጥቤ ባነሣኋቸው ነጥቦች ዙሪያ ነበር የተናገርኩት፡፡ "ሀገርንና ቤተክርስቲያንን አጥቅቷል" ስል ምን ማለቴ እንደሆን በሚገባና ግልጽ በሆነ አማርኛ ለመግለጽ የሞከርኩ መስሎኝ ነበር፡፡ ሰዉ እንዴት መረዳት ተሳነው? እሽ እስኪ አጠር አድርጌ ግልጽ ለማድረግ ልሞክር፡፡

በውቀቱ በቤተክርስቲያን ላይ ጥቃት ፈጽሟል ስል ምን ማለቴ ነው:- ሁሉም ሰው እንደሚረዳው ቤተክርስቲያን ያለ እግዚአብሔር ባዶ ምንምና አገልግሎት ህልውና የሌላት ናት፡፡ ስለዚህ ከምንም በላይ በመጀመሪያ ደረጃ "እግዚአብሔር የለም!" ሲል ህልውናዋን ተፈታተነ ጥቅም አልባ አደረጋት ማለት ነው፡፡ እሱ "እግዚአብሔር የለም!" ብሎ ሲል ቤተክርስቲያን "አለ!" ብላ ትሰብካለችና ስብከቷን ትምህርቷን ሁሉ ውሸት እሷንም ውሸታም ሲያደርጋት ክብሯን አልተዳፈረም? የማስተማሪያ እሴቶቿን ጥቅምና እርባና ቢስ አላደረገም? ከዚህ በላይ ጥቃት መፈጸም ማለት ምን ማለት ነው?

ሌላው ደግሞ አክብራ በያዘቻቸው ቅዱሳኖቿ ተጋድሎ ላይ ሲሳለቅ፣ ቅዱሳንን ሲያዋርድ የቤተክርስቲያንን ጥቅም አልነካም? አልተደፈረም? ጥቃት አልፈጸመም? የቅድስና ማዕረግ ሰጥታ የምታከብራቸውንና የምታስከብራቸውን ቅዱሳን ክብርና ተቀባይነት እንዲያጡ እጅግ በሚገርም የድንቁርና ድፍረት አቡነ ተክለሃይማኖትን "እግር አልባው ባለ ክንፍ" ብሎ በመሳለቅ "...እንግዲህ በሰማዩ ላይ አለቅጥ ሲያተኩር ምድሩን የሚከዳ ምድሩም የምትከዳው ማኅበረሰብ ተክለሃይማኖታዊ ይባላል" በማለት ጨርሶ ምኑም ባልገባው ነገር ላይ የአስተሳሰብ ኪሳራና የውድቀት ምሳሌ አድርጎ ሲመስል፣ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስን የፈጸሙትን ተጋድሎ እየጠቀሰና በተሳሳተ መንገድ እየተረጎመ "የዋህ" ብሎ ሲዘባበትባቸው ቤተክርስቲያን አልተደፈረችም? ጥቅሟ አልተነካም? እንዴት ነው ግን የምታስቡት? ለእናንተ ጥቃት ተፈጸመባት የሚባለው ምን ሲደረግ ነው?

"በሀገር ጥቅም ላይ ጥቃት ክህደት ፈጽሟል ባንዳ ነው" ስል ደግሞ በውቀቱ የምዕራባዊያን ጸሐፍትን ሀገሪቱን ብሔራዊ ጀግና አልባ የማድረግ ሸረኛ ተልዕኮ በማንገብ ይሄንን ሴራ  ለማሳካት የሆነውን በማጋነንና የተለየ ትርጉም በመስጠት፣ የሌለውንም በመፍጠር የዐፄ ቴዎድሮስን ስም ለማጠልሸት እነኙሁ ባዕዳን በከፋት ስም ለማጥፋት የጻፉትን ተሸክሞ አደባባይ በመውጣት ዐፄ ቴዎድሮስን ለማዋረድ ተቀባይነት ለማሳጣት ተደጋጋሚ ጥረት አድርጓል፣ የኢትዮጵያን ስም ለማከፋፋት ይጥሩ እንደነበረ የሚታወቁ ሚሲዮኖችን (መልእክተኞችን) ድሪቶ በመንተት የአማራ ባሕል የታወቀና የሠለጠነ መሆኑ እየታወቀ ምን ዓይነት እንድምታ ሊፈጥር እንደሚችል ፈጽሞ ባለመረዳት አስቂኝ በሆነ መንገድ አማራን የመስለብ ባሕል የነበረው ለማስመሰል ጥሯል ወዘተረፈ. አሁንስ ገብቷቹህ ይሆን?

ሳይንስና ሃይማኖትን ወደ ተመለከቱ ጥያቄዎች ስንሻገር፡- አንዱ ምን አለ "አልቨርት አንስታይንን በእግዚአብሔር ያምናል ያልከው ሐሰት ነው እሱ በሰዋዊ እግዚአብሔር (personal God) አያምንም" አለኝ፡፡ ጠያቂው ይሄ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግን የሚያውቅ አልመሰለኝም፡፡ እሱን የመሰለው አንስታይን በሰዋዊ አምላክ (In personal God) አያምንም ሲባል በፈጣሪ አያምንም ማለት መስሎታል፡፡ እንደዛ ማለት አይደለም፡፡ እኔ ሲጀመር ሰዋዊ ኢሰዋዊ (personal impersonal) ብየ ለይቸ አልተናገርኩም፡፡ በእግዚአብሔር ወይም በፈጣሪ እንደሚያምን ብቻ ነው የተናገርኩኝ፡፡

አንስታይን በሰዋዊ አምላክ **(In personal God)** አላምንም ያሰኘው ለነገረ ሃይማኖት ሩቅ በመሆኑ እንጅ በፈጣሪ ያምነ ሰው ሰዋዊ አምላክን መቀበል የሚያቅተው ሆኖ አልነበረም፡፡ የሰው ልጅ ልዑለ ፍጡራን **(super creature)** እንደመሆኑ **(**ሳይንሱም ወይም መጣቁም ይሄንን ያምናል ብየ ነው**)** እግዚአብሔር እንዲህ ከፍና ለየት አድርጎ ከፈጠረው ፍጥረቱ ጋር ግንኙነት መፍጠር ካስፈለገው ሰዋዊ አምላክ **(personal God)** ሆኖ መቅረቡ ማለትም በሰዎች ላይ የራሱ ፍላጎት **(volition)** ያለው፣ ስሜቶች **(emotions** ለምሳሌ ቁጣ፣ ኃዘን፣መደነቅ መደሰት**)** ፣ ሐሳብ **(intention)** እና ሌሎች ሰዋዊ መለያ ባሕርያትን ተላብሶ መቅረቡ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነውና፡፡ አለዛማ እግዚአብሔር እንደራሱ ማንነት እንደ ሁሉን አዋቂነቱ ነገሮችን ሁሉ አስቀድሞ ያውቃልና ስሜት አልባ ሆኖ ቢቀርብ ከሰው ልጆች ጋር እንዴት መግባባት ይቻላል ታዲያ**?** ወይ ሰዎችንም እንደራሱ ሁሉን አዋቂ ካላደረጋቸው በስተቀር፡፡ ካልሆነ ግን የሰው ልጅ አምላክ እንዳለመሆኑና ዕውቀቱ ችሎታው አቅሙ የተገደበ የተወሰነ እንደመሆኑ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሲቀርብ ኢሰዋዊ ሆኖ ቢቀርብ አለመግባባት፣ እግዚአብሔርን መረዳት አለመቻል ሊፈጠር ነው ማለት ነው፡፡

ስለሆነም እግዚአብሔር የሰው ልጅ እንዲረዳው ከፈለገ ሰዋዊ ሆኖ መቅረቡ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰዋዊ ባሕርያትን ተላብሶ ሰውን ቀረበ ማለት ግን ማንነቱ ሰዋዊ ነው ማለት አይደለም፡፡ ማለትም ስሜቶች **(emotions** ለምሳሌ ቁጣ፣ ኃዘን፣መደነቅ መደሰት**)** ፣ ሐሳብ **(intention)** እና ሌሎች ሰዋዊ መለያ ባሕርያት አሉት ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነውና የሚሆነውን ከመሆኑ በፊት የሚያውቅ ነውና አንድን ነገር ከመሆኑ በፊት ካለማወቁ የተነሣ ሲሆን እንደሚያስገርመው፣ እንደሚያስደንቀው፣ እንደሚያስቆጣው፣ እንደሚያሳዝነው፣ እንደሚያስከፋው፣ እንደሚያኮራው፣ እንደሚያስደስተው ወዘተረፈ። እንደሚያደርገው የሰው ልጅ እሱም ነገሮች ከመፈጸማቸው በፊት ሳያውቅ ቀርቶ ሲፈጸሙ የሰው ልጅ እንደሚሆነው ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ የተቆጣ፣ ያዘነ፣ የተከፋ፣ የተደሰተ፣ የተደነቀ፣ የተገረመ መስሎ የሚቀርበው ሰው የሚረዳው እንደዛ ሆኖ ሲቀርብ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ በሰዋዊ አምላክ የማያምኑ ሰዎች ያልተረዱት ነጥብ ይሄንን ነው፡፡

ሌላው በምዕራቡ ዓለም ውስጥ ሰዎችን በሰዋዊ አምላክ እንዳያምኑ ያደረጋቸው ጉዳይ እነሱ አንቀበላቸውም የሚሏቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ስሞችና ይዘታቸው እነቀበለዋለን በሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተጠቅሰው እያለ የመጻሕፍት ቅዱሳትን ቁጥር ገድበው መጽሐፍ ቅዱስ እነኝህ ብቻ ናቸው ማለታቸው፣ ተጨማሪዎችንና አዋልዳትን አለመቀበላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይሄ ብቻ ነው ብለው በያዙት መጽሐፍ ሊያገኙት የሚፈልጉትን መልስ እዛው አለማግኘታቸው፣ እርስ በእርሱ የሚጋጭና ስሕተቶች ያሉበት መስሎ ሊታያቸው በመቻሉ ነው ሰዋዊ አምላክን ለመቀበል እንዳይችሉ ያደረጋቸው፡፡ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምላሾቹ፣ እርስ በእርሱ የሚጋጭና ስሕተት ለሚመስላቸው ቃል ሁሉ ባልተቀበሏቸው ተጨማሪና አዋልዳት ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ምላሻቸው በሚገባ ተቀምጧልና፡፡ ለምሳሌ "…እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ" ዘፍ. 6፣5

ይሄና ይሄንን የመሰሉ ገለጻዎች በሰዋዊ አምላክ የማያምኑ ሰዎችን አሰናክሏል፡፡ "እንዴት እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ሆኖ እያለ አስቀድሞ አያውቀው እንደነበረ ሁሉ አዘነ ተጸጸተ ይላል?" ብለውም ይጠይቃሉ፡፡ ጥያቄው አግባብነት ያለው ጥያቄ ነው፡፡ መልሱም አስቀድሜ እንዳልኩት ነው፡፡ የሰው ልጅ የኃጢአት ሥራው እግዚአብሔርን እጅግ እንዳስቆጣው እንዳሳዘነውና ከዚህ ግብር እንዲመለስ ለራሱ ለሰው ልጅ መልእክት መተላለፍ ካለበት መልእክቱ መተላለፍ ያለበት በዚህ መንገድ ስለሆነ እንጅ በቃሉ ላይ እንደተገለጸው

የሰው ልጅ እጅግ በኃጢአት የሚጎድፍ መሆኑን እግዚአብሔር አስቀድሞ ሳያውቀው ቀርቶ አይደለም፡፡ ሊቀ ለቢያት ሙሴ ይሄንን ቃል የተጠቀመው ሰዎቹ የሠሩት ኃጢአት ምን ያህል የከበደ እንደነበር ለማስገንዘብ ፈልጎ እንጅ የሆነው ነገር እግዚአብሔር እንዲሆን የማይፈልገው ቢሆንም በእርግጥም በድርጊቱ እግዚአብሔር እንደዚያ ሆኖ አይደለም፡፡

ሌላው መሰናከያቸው ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመረዳት ኢሳ. 7፣14, ማቴ. 1፣23 ጌታ ያለ ወንድ ዘር ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ያምናል፡፡ እንኳን ክርስቲያን እስምላሞችም ያለወንድ ዘር በድንግልና መወለዱን ያምናሉ፡፡ ጉዳዩ ይሄ ሆኖ ሳለ ማቴ. 1 ላይ የጌታ የዘር ኃረግ ሲቆጠር ልክ የዮሴፍ ልጅ እንደሆነ ሁሉ ትውልዱ በዮሴፍ አረጋዊ በኩል መቆጠሩ "ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግልና የተወለደ መሲሕ አይደለም ማለት ነው" የሚል ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡

ይሄ እንዴት ሊሆን እንደቻለ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት በግራኝ አሕመድ ወረራ ቅዱሳት መጻሕፍት ጠፍተው ተቃጥለው ወድመው ስለነበረ መጻሕፍቱን መልሶ ለመተካትና  እያመሰጠሩ በተብራራና የተሳሳተ እርስ በእርሱ የሚጋጭ የሚመስለውን ቃል ሁሉ ለምን እንደዚያ እንደሆነና መተስማማ መልኩ በአንድምታ ትርጓሜ አብራርቶ ለመመለስ ሊቃውንቱ በዐፄ ፋሲል ዘመን ከመላ ሀገሪቱ ተሰብስበው ጎንደር ላይ በመከተትና ጽኑ ሱባኤ በመያዝ  ቸሩ እግዚአብሔር ከፍጥረተ ዓለም እስከ ኅልቀተ ዓለም ያለውን ነገር ሁሉ ገልጾላቸው ሁሉንም መጻሕፍት ጥሬ ቃሉ እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉንም አመስጥረው እያብራሩና እያስማሙ ተርጉመዋል፡፡

በዚህም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን "መጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት ያለበትና እርስ በእርሱ የሚጋጭ ቃል ያለበት መጽሐፍ ነው" የሚል ስም ተሰጥቶት ክርስትና ተጋፍጦት ከነበረው ያለመታመን አደጋ ታድጋለች፡፡ የአንድምታ ትርጓሜ ከተሰጣቸው በኋላ እነዚህ መጻሕፍት ሊቃውንቱ ወደ ኢየሩሳሌምና ሮም በሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉዞ፣ ሐዋርያዊ ተልእኮም ሆነ በስርቆትም በምንም እየሔዱ ያልገቡበት የምዕራቡ ዓለም ክፍል የለም፡፡ እነኝህ የእኛ ቤተክርስቲያን የትርጓሜ መጻሕፍት ሐዋርያው ማቴዎስ የጌታን የዘር ኃረግ በዮሴፍ በኩል የቆጠረበትን ምክንያቶች ሲተነትኑ አንዱና ዋነኛው የዮሴፍና የእመቤታችን አያት አንድ በመሆኑና ዝምድና ያላቸው በመሆኑ እንደሆነ ማን ቢወልድ ማን የሚለውን ጨምረው በመዘርዘር ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ የዘር ግንዳቸው አንድ በመሆኑ ነው በዮሴፍ በኩል የተቆጠረው፡፡

ዝምድና ያላቸው ከሆነ ለምን ታዲያ ቅድስት ድንግል ማርያም ለዮሴፍ ታጨች የተባለ እንደሆነ ወትሮም ቢሆን ለዮሴፍ የታጨችው ሊያገባት ሳይሆን እጮኝነት ሳትሰጥ ጌታን ብትፀንስና "በድንግልና ነው የፀነስኩት" ብትል ስለማያምኑ ስለማይቀበሏትና በሕጋቸውም መሠረት ዘኍ. 5፣19 መሠረት ያለባል ወይም እጮኛ በዝሙት ፀንሳ የተገኘች ሴት በድንጋይ ተወግራ እንድትሞት ስለሚደረግ ወላዲተ አምላክን ከእንዲህ ዓይነት የአይሁድ ፈተና ለመጠበቅ ታስቦ ፀንሳ ሲያዩዋት የዮሴፍ ነው ብለው እንዲያስቡ የተደረገ እንጅ እንዲያገባት አይደለምና ነው ይሄንን የእግዚአብሔር ምሥጢር የሚያውቁ ካህናት በምሥጢር ለዘመዷ ለዮሴፍ እንደታጨች አድርገው የሰጧት፡፡ በዚህም ምክንያት ነው አይሁድ ጌታ ከዮሴፍ የተወለደ ሩቅ ብእሲ የመሰላቸውና ጌታን "የዮሴፍ ልጅ" ሲሉ የሚጠሩት ማቴ. 13፣55

ሌላው ጥርጣሬ የፈጠረባቸው ጌታ ሰው ሆኖ ስለመወለዱ ያለው ነገር ነው፡፡ እነሱ መጽሐፍ ቅዱስ ይሄ ብቻ ነው በሚሉት መጽሐፍ ውስጥ ጌታ መቸና የት? እንዴት ከሰው ተወልዶ እንደሚያድነው ለአዳም ቃል ኪዳን እንደገባለት የሚናገር የሚያስረዳ ቃል የለም፡፡ ጌታ

መወለዱን ግን በመጸሐፍ ቅዱስ የተለያየ ክፍል ስለተጠቀሰ ያምናሉ፡፡ መቸ? የት? እንዴት? ከማን ጋር ቃልኪዳን በገባው መሠረት? ለምንስ ነው ጌታ የተወለደው? ለሚሉት ጥያቄዎች ግን እነሱ መጽሐፍ ቅዱስ ይሄ ብቻ ነው የሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ መልስ አይሰጥም፡፡ ይሄንን መልስ የምናገኘው ቤተክርስቲያን በያዘቻቸው ቅዱሳት መጻሐፍት ነው፡፡

ዘፍጥ. 4 ላይ አዳም ሔዋንን እንዳወቃት ቃየንንና አቤልን እንደወለደች ቃየን በቅናት ወንድሙን አቤልን እንደገደለው ይተርክና ቁ. 17 ላይ "ቃየንም ሚስቱን አወቀ ፀነሰችም ሄኖሕንም ወለደች" ይላል፡፡ ይህች ሴት ከየት መጣች? በምድር ላይ ያሉት አራት ሰዎች ብቻ ነበሩ አቤል ሲሞት ሦስት ሰው ይቀራል ሴት እንደተወለደች አልተገለጸም ታዲያ ከየት መጣች?

እናም እነሱ መጽሐፍ ቅዱስ ይሄ ብቻ ነው ብለው በያዙት የ 66 ቅዱሳት መጻሕፍት ጥራዝ ላይ እንዲህ ዓይነት በርካታ ስሕተት የሚመስልና እርስ በእርሱ የሚጋጭ የሚመስል ቃል ያለበት በመሆኑ ከዚህ የተነሣ ከሃይማኖት ሊርቁና ሰዋዊ እግዚአብሔርን የማያምኑ ወገኖች እንዲወጡ አድርጓቸዋል፡፡

እንጅ አንስታይን በእግዚአብሔር የሚያምን እንደሆነ ራሱ አንስታይን ከተናገራቸው ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

**"I'm not an atheist and I don't think I can call myself a pantheist. We are in the position of a little child entering a huge library filled with books in many languages. The child knows someone must have written those books. It does not know how. It does not understand the languages in which they are written. The child dimly suspects a mysterious order in the arrangements of the books, but doesn't know what it is. That, it seems to me, is the attitude of even the most intelligent human being toward God." G. S. Viereck, *Glimpses of the Great* (Macauley, New York, 1930), quoted by D. Brian, *Einstein: A Life* , p. 186.**

"እኔ በእግዚአብሔር የማላምን ሰው አይደለሁም! እራሴን ጴንጤ ብየ መጥራት የምችልም አይመስለኝም፡፡ እኛ በተለያዩ ቋንቋዎች በተጻፉ መጻሕፍት በተሞላ ቤተመጻሕፍት ውስጥ በሚገባ ሕፃን ቦታ ላይ ነው ያለነው፡፡ ሕፃኑ መጻሕፍቱን የሆነ ሰው የጻፋቸው መሆን እንዳለባቸው ያውቃል፡፡ እንዴት እንደሆነ አይታወቅም፣ የትኞቹ መጻሕፍት በምን ቋንቋ እንደተጻፉም አይረዳም፡፡ ልጁ በቀላሉ በመጻሕፍቱ አደረጃጀት ላይ ምሥጢራዊ ቅደም ተከተል እንዳለ ይጠረጥራል፡፡ ነገር ግን ምን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ የመጨረሻ ምሁር አዋቂ የምንለው የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ዘንድ ለእኔ የሚመስለኝ እንደዛ ነው" ነበር ያለው፡፡

አንስታይን ሳይንስን (መጣቅን) በሕጻን ልጅ መስሎ ሳይንስ (መጣቅ) ስለ እግዚአብሔር ምንም የማያውቅና የማወቅም አቅም እንደሌለው እንዴት ድንቅ በሆነ አገላለጽ እንደገለጸው አያቹህ? ሳይንስ ማለት ባልተጨበጠ ነገር የማያምን እንደሆነ ይነገራል፡፡ ለዚህ መርሕ ታማኝና ተገዥ የሆነ ሰው የሚያየውን ነገር ማስተዋል መረዳት ተስኖት የእግዚአብሔር መኖር የተጨበጠ አይደለም የሚል ከሆነ "የለም!" የሚለውም የተጨበጠ አይደለምና "የለም!" ብሎ አቋም መያዝ አይችልም፡፡

**"In view of such harmony in the cosmos which I, with my limited human mind, am able to recognize, there are yet people who say there is no God. But what really makes me angry is that they quote me for the support of such views." Prinz Hubertus zu Lowenstein, *Towards the Further Shore: An Autobiography* (Victor Gollancz, London, 1968), p. 156.**

"በእንዲህ ያለ ዕያታ በዓለማተ ሕዋ (cosmos) ውስጥ እኔ፣ በእኔ ውስን የሰው አእምሮ ገና አሁንም እግዚአብሔር የለም የሚሉ ሰዎች መኖራቸውን መገንዘብ ችያለሁ፡፡ ነገር ግን በእውነት የሚያበሳጨኝ ነገር ቢኖር ለእንዲህ ዓይነት ዕይታዎች ድጋፍ እኔን መጥቀሳቸው ነው" በማለት ተናግሯል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ "በእግዚአብሔር አላምንም! እግዚአብሔር የለም!" የሚሉ ሰዎች "ሞኝና ወረቀት ያሲያዙትን አይለቅም" እንዲሉ እንዲሁ በድርቅና "እግዚአብሔር የለም!" ይላሉ እንጅ ተጨባጭ በሆነ መንገድ "በዚህ በዚህ አመክንዮ፣ በዚህ በዚህ ተጨባጭ ማስረጃ እግዚአብሔር የለም!" ብሎ ይህ የሚያስበው ነገር እውነት ስለ መሆኑ ሊያረጋግጥ የቻለ አይደለም የሞከረ እንኳን አንድም ሰው አላጋጠመኝም፡፡ ሁሉም ሲባል ስለሰማ ብቻ ተለጣፊ ሆኖ የሚያራግበው እንጅ ትንሽም እንኳን የመሰለው ነገር ኖሮ ያንን እንደሚልና ይሄንንም መግለጥ ማስረዳት የቻለ የሞከረ አንድም ሰው የለም፡፡ በጣም አሳፋሪ ነገር ነው፡፡

እንዲህ የሚሉ ሰዎች እንዲህ የሚሉበትን ምክንያት ባለፈው ጠቆም አድርጌ ነበር፡፡ ይህ አባባላቸው አንዳች እውነት ወይም ተጨባጭ ነገር ያለው ሐሳብ ሆኖ ሳይሆን ከዐመፃ የተነሣ የሚራገብ ደካማ ሐሳብ ነው፡፡ ያንን የሚሉ ሰዎች ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ በሃይማኖት፣ በባሕል፣ በሞራል (በቅስም) ድንጋጌዎች ማድረግ ከሚፈልጉት ነገር መከልከል የማይፈልጉ ስሜታቸው ያዘዛቸውን ነገር ሁሉ በነጻነት ማድረግ የሚፈልጉ የስሜት ባሮች ናቸው፡፡

አንድ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር ግብረገብነት ሥነምግባር የሌላቸው ዘልዛሎችና ኃላፊነት የማይሰማቸው መሆናቸው ነው፡፡ ነውር የሚባል ነገር አያውቁም፣ ወሲብ እንደመዝናኛነቱ የትም ከማንም ጋር መደረግ እንዳለበት ይሰብካሉ፣ ትዳር የሚለውና አብሮት ያለው ኃላፊነት ጨርሶ አይታያቸውም ይቃወሙታልም፡፡

ፍልስፍና ነው ብለው በሚያወሩትና በሚኖሩት የሕይዎት ዘይቤ ሕዝብ እነሱን አርዓያ አድርጎ ተቀብሎ የሚከተላቸውና በእነሱ የሕይዎት ዘይቤ የሚኖር ቢሆን ኖሮ የሰው ልጅ ከምድረ ገጽ ሊጠፋ እንደሚችል አያውቁም፡፡ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ፍጡር እንደመሆኑ ሰላሙና ደኅንነቱ ተጠብቆ እንዲኖር የሚያስችሉትን እንደ ሃይማኖት፣ ባሕል፣ የሞራል (የቅስም) ድንጋጌዎች ያሉ የጋራ ጥቅሙ የማስጠበቂያ መንገዶቹ ባይኖሩ ኖሮ ሰው እንደ አውሬ ተባልቶ ሊጠፋፋ ይችል እንደነበረ እነኝህ ፍልስፍናን የደካማነታቸውና የባለጌነታቸው መሸፈኛ ያደረጉት ደናቁርት ፈጽሞ አይገባቸውም፡፡

“እግዚአብሔር የለም!” የሚሉበት ምክንያትና ዓላማም ይሄው ነው ልቅ መደዴ ለመሆን እንጅ አባባሉ ተጨባጭነት ስላለው አይደለም፡፡ ተፈላስፈው ሞተው አንድ የሚሉት አባባል አላቸው “እግዚአብሔር ፈጣሪ ከሌለው ተፈጥሮም ያለፈጣሪ መገኘት ይችላል” ይላሉ፡፡ እግዚአብሔር ፈጣሪ ካለውማ ፍጡር እንጅ ፈጣሪ አይደለም እኮ! ይህ አባባለቸው ለእግዚአብሔር እግዚአብሔር አሁንም እንደገና ለእግዚአብሔር ሌላ እግዚአብሔር አለው አሁንም እንደገና ለፈጣሪ ፈጣሪ በማበጀት ማለቂያ የሌላቸው እግዚአብሔሮች ነው ያሉት ማለታቸው እንደሆነ አልገባቸውም፡፡ አስተሳሰባቸው በጣም ያልበሰለ ነው፡፡

የሃይማኖት፣ የባሕል፣ የሞራል (የቅስም) ድንጋጌዎች ይኖሩ ዘንድ ግድ የሆነበት ምክንያት በሰው ልጆች ላይ አላስፈላጊ ጫናና ዕቀባ ለማሳደር ተፈልጎ ሳይሆን አካላዊና ሥነልቡናዊ ጤንነቱ ተጠብቆ የሰው ልጅ እንደማኅበራዊ ፍጡርነቱ ህልው ሆኖ እንዲኖር ነው፡፡ የሃይማኖት፣ የባሕል፣ የሞራል (የቅስም) ድንጋጌዎች ይዘት ትኩረትና ትምህርታቸውም የሰው ልጅ አውሬያዊ ማንነቱን ገትቶ እየተከባበረ፣ እየተሳሰበ፣ እየተፋቀረ፣ እየተረዳዳ፣ እየተዛዘነ፣ እየተደጋገፈ፣ እየተቻቻለ፣ ይቅር እየተባባለ እንዲኖር ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ግን ይሄንን መረዳት የሚችል አቅም የላቸውምና መረዳት አልቻሉም፡፡

እዚህ ላይ የአንደኛው የሃይማኖት ድንጋጌ ከሌላኛው ጋር ባሕሉም እንደዛው የሚቃረን መሆኑን አጥቸው አይደለም፡፡ ለምሳሌ የሴቶችን አያያዝና ጋብቻን በተመለከተ ክርስትናና እስልምና ያላቸው ልዩነት በጣም ሰፊ ነው፡፡ እኔ ከላይ ያልኩትን ያልኩት ግን ቀደም ሲል በኦሪቱ በኋላም በሐዲሱ ያለውን ሃይማኖታዊ ድንጋጌ በማሰብ ነው፡፡

ተፈላሰፍን እያሉ በሚያደርጉት ፀረ ሞራል (ቅስም) ፀረ ሃይማኖትና ፀረ ባሕል ድርጊቶች የዋህንን እያሰናከሉ በሀገር ላይ ከንቱ ዜጋ እንዲበራከት ሀገር እንድትከስር ያደርጋሉ፡፡ እዚህ ሀገራችንም (ሙት ወቃሽ ለመሆን አይደለም) አንዳንዶቻቹህ ታውቁ ይሆናል፤ ወጣቶች ስብሐቲዝም (ስብሐታዊነት) የሚሉት ንጽሕናን ያለመጠበቅ፣ የሱሰኝነትና የዘልዛላነት እንቅስቃሴን እስከመመሥረት ድረስ የደረሰ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔርን የከንቱነት እንቅስቃሴ ምሳሌና አርአያ አድርጎ የሚደረግ እንቅስቃሴ ሁሉ ተፈጥሮ ነበር አሁንም አለ፡፡ ሰውየው ምንም የማያውቁ ወጣቶች በዚህ ደረጃ ዘቅጠው እየሳቱ እያየ ከንቱ ነገርን እየተናገረ ይሄንን ድርጊቸውን ያበረታታ ነበር እንጅ “ተው አይጠቅምም!” ብሎ ሊገስጽ አልቻለም፡፡

ወደ ሌላው ጥያቄ ስናልፍ፡- ስለ ፍየል እባብን መብላት የተናገርኩትን “ተረት ተረት ነው እንጅ እውነት አይደለም!” የሚል ነው፡፡ ይሄንን ያለው ሰው ይሄንን ከማለቱ በፊት በቀላሉ አንድ የፍየል እረኛን ቢጠይቅ በዓይኑ ያየውን ነገር በነገረውና እውነቱን ማረጋገጥ በቻለ ነበር፡፡ እንዳልኳቹህ ለእኛ ቀረብ የሚለውን ለመጥቀስ እንጅ ግሩም የሱ ሥራ ኧረ ከዚህ የበለጠ ስንት የሚደንቅ ነገር አለ እኮ መሰላቹህ!

የሚያዩትን ለማያስተውሉት እግዚአብሔር አልቦዎች እስኪ ቅርብ ከሆኑት አንድ ሁለት ምሳሌ ልጨምርላቸው፡፡ ግመልን ታውቋታላቹህ አይደል? የበረሀው መርከብ በመባል ትታወቃለች፡፡ የእሷ አገልግሎት ባትኖር ኖሮ የሰው ልጅ በበረሀ ለመኖር አይችል እንደነበር ይገለጣል፡፡ ይህችን እንስሳ እግዚአብሔር ለበረሀ እንዴት አመቻችቶ እንደፈጠራት እንመልከት፡፡ እግሯ እረዝሞ የቁመቷ ቀፍ ማለት ዋእዩን ወይም የመሬቱን ግለት ለመቋቋም እንድትችል ታስቦ ነው፡፡ የሰኮናዋ መሰፋት በረሀ አሸዋማ ስለሆነ እግሯ አሸዋ ውስጥ እየሰጠመ እንዳትያዝ ታስቦ ነው፡፡ ከሁሉም የሚደንቀው ደግሞ በረሀ የውሀ ችግር ስላለ ይሄ ሁኔታ አገልግሎቷን እንዳያሰናክል ሲጠማት ከዚያ እየወሰደች ረጅም ጊዜ ውኃ ሳትጠጣ መቆየት እንድትችል ጀርባዋ ላይ የውኃ ማስቀመጫ ማሰሮ ሠርቶላታል፡፡ ይሄ ጀርባዋ ላይ እንደሻኛ ጉብ ብሎ ተነፍቶ የምታዩት ነገር አለ አይደል? እሱ ነው የውኃ ማስቀመጫ ማሰሮዋ፡፡

ጣና አንድ የማውቀው ጌርጌሶ የሚባል ግዙፍ ነጭ ወፍ አለ፡፡ በብዙዎች ዘንድ ይታወቃል፡፡ ምግቡ ዓሣ ነው ውኃ ላይ ነው ውሎው፡፡ ዓሣዎች ብቅ ሲሉ ለቀም እያረገ እየተመገበ ይኖራል፡፡ እግዚአብሔር ይሄንን ወፍ ምግቡን ዓሣ ሲያደርግለት ተፈጥሮውን ከውኃው ጋር ማስማማቱ ግድ ነውና እንዴት አስማማው መሰላቹህ፤ ከባሕሩ ብቅ የሚሉ ዓሣዎችን ለመመገብ በሚያደርገው ጥረት ጭንቅላቱ እየጠለቀ ለአደጋ እንዳይዳረግ መንቁሩን በጣም አስረዘመለት፡፡ ውኃው ላይ ማረፍና አኮብኩቦ መነሣት እንዲችልም የእግሩ ጣቶች እንደሌላው ወፍ ሆኖ ግን በጣትና ጣት መሀል ያለውን ክፍተት ተጣጣፊ ለስላሳ ግን ጠንካራ ቆዳ ሸፈነው፡፡

ይሄ በመሆኑም በሮ መጥቶ ውኃው ላይ ሲያርፍ ውኃው ውስጥ ሳይጠልቅ ተንሸራቶ ለማረፍ አስችሎታል፡፡ ሲነሣም ልክ ሲያርፍ እዳደረገው የጫፍና ጫፍ ረጃጅም ጣቶቹን ወደ ጎንና ጎን ለጥጦ ይዘረጋቸውና ውኃውን በእግሩ እየመታ እንደማኮብኮብ እያለ ጥቂት ርቀት ከተጓዘ በኋላ ለመብረር ይችላል፡፡ ይሄንን እንዲያደርግ ያስቻለው ጣቶቹ ለምሳሌ እንደ ዶሮ ጣቶች በጣትና ጣቱ መሀል ክፍት ሳይሆኑ ከላይ ባልኳቹህ ቆዳ መሰል ነገር የተሸፈነ በመሆኑ ነው፡፡ ዳክዬና ሌሎች ሕይዎታቸው ውኃ ላይ የተመሠረተላቸው አእዋፍም እግራቸው እንዲሁ ነው፡፡ ሁሉም ነፍስ ያለው ፍጡር ሁሉ ምግቡ የሆነለትን ነገር ለመመገብ እብዲችል ተደርጎ በድንዮ ጥበብ ተመቻችቶ የተፈጠረ ነው፡፡ ለጌርጌሶ የአንበሳ አፍና ጥርስ ቢሰጠው ኖሮ ዝርያው ይጠፋ ነበር እንጅ ህልውናው አይቀጥልም ነበር፡፡ ሌላውም እንደዛው፡፡

ባሕር ውስጥ ያሉ ዓሣዎችን ብናይ ሲመገቡና ሲተነፍሱ ውኃው ሆዳቸው ውስጥ እየገባ ችግር እንዳይፈጥርባቸው እንዴት ባለ ድንቅ የአሠራር ዘዴ (መካኒዝም) የሰውነት አካላቸው ሥራውን እንዲከውን ማድረግ እንዲችል እንዳደረገ ብታዩ ደንቋቹህ አያበቃም፡፡

እንግዲህ እነዚህ ፍጥረታት ይሄንን ያህል እያሰበ ከሚኖሩበት ሁኔታ ጋር በድንቅ ጥበብ አስማምቶ የፈጠራቸው ሳይኖር እንዴት ሊገኙ ቻሉ? ራሳቸው እራሳቸውን እንዳልፈጠሩ ግልጽ ነውና የዚህ ረቂቅ ሥራ ባለቤትና ፈጣሪ የለውም ማለት እንዴት ይቻላል ጃል?

ባለፈው ጽሑፌ እነዚህን "እግዚአብሔር የለም!" ባይ ድኩማንን የእግዚአብሔርን መኖር ለማስረዳት እንዲህ ዓይነት ምሳሌዎችን ተጠቀምኩ እንጅ ከመጽሐፍ ቅዱስ የጠቀስኩት አንድም ጥቅስ እንዳልነበረ ታስታውሳላቹህ፡፡ ይሄንን ለምን እንዳደረኩ ያልገባው አንድ ወንድሜ ምን አለኝ መሰላቹህ "ፍጥረተ ዓለሙ በፈጣሪ የተሠራ መሆኑን ቁርአናዊ መረጃዎችን ላቀርብልህ እችላለሁ" አለኝ፡፡ እግዚአብሔር የለም ባዮች መጽሐፍ ቅዱስን አለመቀበላቸው ነው እንጅ ችግሬ መጽሐፍ ቅዱስን የሚቀበሉ ቢሆን ኖሮማ ከዘፍጥረት እስከ የዮሐንስ ራዕይ የሚናገረው ይሄንኑ አልነበረም እንዴ! መጽሐፍ ቅዱስን ስለማይቀበሉ እኮነው እነዚያን ምሳሌዎችና አመክንዮዎች ለመጠቀም የተገደድኩት ወዳጄ!

ሌላው ዩኒቨርስ የሚለውን ቃል ፍጥረተ ዓለም ስል እንደተረጎምኩት ታስታውሳላቹህ፡፡ የዚህ ምክንያት በግእዝ እግዚአብሔር የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም አለው፡፡ አንደኛው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አኳያ አብ ወልድ መንፈስ ቅድስ ተወክለው ያሉበት ስም ነው፡፡ እግዚ ጌታን ወይም ወልድን ይወክላል፡፡ አብ አባትን ወይም አብን ይወክላል፡፡ ሔር መንፈስ ቅዱስን ይወክላል፡፡

ሌላው ትርጉሙ ደግሞ ስሙ ከሁለት ይከፈልና እግዚአ የሚለው ቃል ጌታ ይሆንና ብሔር ደግሞ ሀገር ይሆናል፡፡ የሀገር ጌታ ፈጣሪ ገዥ ማለት ነው፡፡ አጠቃላዩን ፍጥረት እንደ አንድ ሀገር ቆጥሮ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም አጠቃላዩን ፍጥረት (ዩኒቨርስን) እግዚአብሔር ከሚለው የፈጣሪ ስም ጋር ለማስማማት እንደ አንድ ዓለም ወሰድኩትና ዩኒቨርስ የሚለውን ቃል ፍጥረተ ዓለም በሚል ተስተካካይ ቃል ተረጎምኩት ማለት ነው፡፡ ግእዙ ፕላኔቶችን ዓለማት ነው የሚላቸው፡፡ ባለፈው ዐበይተ ከዋክብት ብየ ተርጉሜው ነበር ስሕተት ነው፡፡ ሳይንስ (መጣቅ) የሚያውቃቸው ዘጠኙን ብቻ ነው ቤተክርስቲያን የምታውቃቸው ሳይንስ (መጣቅ) ገና ያልደረሰባቸው 13 ዓለማት (ፕላኔቶች) አሉ በፈሊጥ በነፍሳት ሥያሜ የሚጠሩ፡፡ ይሄው ነው እንግዲህ ጥያቄዎቻቹህ ተደጋጋሚ ናቸው በተቻለኝ መጠን ለሁሉም ለመመለስ እንደሞከርኩ አስባለሁ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርዳው

amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com